# ትምህርት 3

1. እግዚአብሔር በመጽሐፉ ውስጥ እንዲጻፍ ያደረገው የመጀመሪያው ቃል ምን የሚል ነው?

ሀ- እግዚአብሔር በመጽሐፉ ውስጥ እንዲጻፍ ያደረገው የመጀመሪያው ቃል፤ «በመጀመሪያ» የሚል ነው።

2. እግዚአብሔር ቃሉን «በመጀመሪያ» በሚል ለምን ጀመረ?

ሀ- ምክንያቱም ሁሉም ነገር መጀመሪያ እንዳለው እንድናውቅ እግዚአብሔር ስለሚፈልግ ነው።

3. ከመጀመሪያ በፊት ወንዞችና ሐይቆች ነበሩ?

ሀ- አልነበሩም።

4. ከመጀመሪያ በፊት ተራሮችና ዛፎች ነበሩ?

ሀ- አልነበሩም።

5. ከመጀመሪያ በፊት ፀሐይ ጨረቃና ከዋክብት ነበሩ?

ሀ- አልነበሩም።

6. ከመጀመሪያ በፊት እንስሳትና ወፎች ነበሩ?

ሀ- አልነበሩም።

7. ከመጀመሪያ በፊት ሰማይና ምድር ነበሩ?

ሀ- አልነበሩም።

8. ከመጀመሪያ በፊት ነጭ ወይም ጥቁር ሕዝብ ነበር?

ሀ- አልነበረም።

9. ከመጀመሪያ በፊት መናፍስት ነበሩ?

ሀ- አልነበሩም።

10. ከመጀመሪያ በፊት ብቻውን ይኖር የነበረው ማን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ነው።

11. ከመጀመሪያ በፊት እግዚአብሔር ብቻውን ከኖረ ከሁሉም የሚበልጠው ማን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ነው።

12. ስለ መጀመሪያ እውነቱን ሊነግረን የሚችለው ማን ነው?
ሀ- እግዚአብሔር ነው፤ምክንያቱም ከመጀመሪያ በፊት የነበረው እርሱ ብቻ ስለሆነ ነው።

13. ስለ መጀመሪያ እውነቱን ሊነግረን የሚችለው ማን ነው?
ሀ- እግዚአብሔር ነው፤ምክንያቱም ከመጀመሪያ በፊት የነበረው እርሱ ብቻ ስለሆነ ነው።

14. እግዚአብሔር መኖር የጀመረው መቼ ነው?

ሀ- እግዚአብሔር መጀመሪያ የለውም።

ለ- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ይኖራል።

15. እግዚአብሔርን የፈጠረው ይኖር ይሆን?

ሀ- የለም።

ለ- እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው።

16. እግዚአብሔር ያልነበረበት ጊዜ ነበር?

ሀ- አልነበረም።
ለ- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ነበር።
ሐ- እግዚአብሔር ሁልጊዜም አለ።
መ- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ይኖራል።

17. ሰዎች ለመኖር ምግብና ውሃ ያስፈልጋቸዋል፤ እግዚአብሔር ለመኖር የሚያስፈልገው ምንድን ነው?
ሀ- እግዚአብሔር ለመኖር ምንም አያስፈልገውም።

18. ታዲያ እግዚአብሔር የሚኖረው እንዴት ነው?
ሀ- እግዚአብሔር የሚኖረው በራሱ ኃይል ነው።

- እግዚአብሔር የሚበላው ምግብና የሚጠጣው ውኃ የማያስፈልገው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር እንደሰው አካል ስለሌለው ነው።

- እግዚአብሔር ለማየት የፀሐይ ብርሃን የማያስፈልገው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር እንደሰው አካል ስለሌለው ነው።

- እግዚአብሔር ለመራመድ ምድር ያላስፈልገው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር እንደሰው አካል ስለሌለው ነው።

- እግዚአብሔር ሥጋ አለው?
- የለውም።

- እግዚአብሔር አጥንት አለው?

- የለውም።

- እግዚአብሔር ደም አለው?
- የለውም።

- እግዚአብሔር ሥጋ ወይም አጥንት ወይም ደም የለውም።

- እግዚአብሔር ሥጋ ወይም አጥንት ወይም ደም ከሌለው ታዲያ እግዚአብሔር ምንድን ነው?

- እግዚአብሔር መንፈስ ነው።

- እግዚአብሔር መንፈስ ነው ማለት ምን ማለት ነው?
- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡-

- ነፋስን ልታዩት ትችላላችሁ?
- አዎን አትችሉም።

- ታዲያ ነፋስ አለ?
- አዎን አለ።

- ነፋስን ልታዩት እንደማትችሉት ሁሉ፣ እግዚአብሔርንም ማየት አትችሉም።

- ነገር ግን ነፋስ እንዳለ ሁሉ፣ እግዚአብሔርም አለ።

- እግዚአብሔርን ማየት ባትችሉም እንኳን እርሱ ግን አለ።

- እግዚአብሔር የት ነው ያለው?

- እግዚአብሔር የት እንዳለ ሊነግረን የሚችለው እርሱ ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር በመጽሐፉ ውስጥ እንደሚናገረው እርሱ በሁሉም ስፍራ አለ።

- እግዚአብሔር እንደሚናገረው፣ እርሱ ሁል ጊዜ በሁሉም ስፍራ አለ።

- እግዚአብሔር በሰማይ አለ።
- እግዚአብሔር በምድርም አለ።

- እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ በአዲስ አበባ አለ።
- እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ በአርባ ምንጭ አለ።
- እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ በጂንካ አለ።

- እግዚአብሔር አሁን እዚህ አለ።
- እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በሁሉም ቦታ አለ።

- አንድ ሰው በአንድ ጊዜ በአሜሪካና በአፍሪካ ሊገኝ ይችላል?
- አይችልም።

- የማይችለው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ሰው ሥጋና ደም ስላለው ነው።

- ሰው በአንድ ጊዜ በአንድ ስፍራ ብቻ ነው መገኘት የሚችለው።

- እግዚአብሔር ሥጋና ደም ስለሌለው ሁል ጊዜ በሁሉም ስፍራ መሆን ይችላል።

- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ መሆን የሚችለው እርሱ መንፈስ ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በሁሉም ስፍራ አለ።

- በቤት ውስጥ ብትሆን ከአንተ ጋር ማን አለ?
- እግዚአብሔር አለ።

- ወደ ሥራ ስፍራ ብትሄድ ከአንተ ጋር ማን አለ?
- እግዚአብሔር አለ።

- ወዳጅህን ለመጎብኘት ብትሄድ እዚያ ከአንተ ጋር ማን አለ?
- እግዚአብሔር አለ።

- እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በሁሉም ሥፍራ መሆን ይችላል።

- ከእግዚአብሔር ለመደበቅ ወዴት መሄድ እንችላለን?

- ከእግዚአብሔር ልንደበቅ አንችልም።

- ሁልጊዜ በሁሉም ስፍራ ከሚገኝ ከእግዚአብሔር ልንሰወር እንችላለን?

- በፍጹም አንችልም።

- ከፍ ወዳለው ተራራ ሄደን ለመደበቅ ብንሞክር፣ ከእግዚአብሔር ልንሰወር እንችላለን?

- አንችልም።
- እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ አለ።

- በቤታችን ውስጥ ባለው ጥግ ስፍራ ልንደበቅ ብንሞክር ከእግዚአብሔር ልንሰወር እንችላለን?

- አንችልም።
- እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ አለ።

- በደን ውስጥ ብንሸሸግ ከእግዚአብሔር ልንሰወር እንችላለን?

- በፍጹም አንችልም።

- እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ አለ።

- የቱንም ያህል ብርቱ ሙከራ ብናደርግ፣ ከእግዚአብሔር ልንሰወር አንችልም።

- ለምን?
- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በሁሉም ስፍራ ስላለ ነው።

- አንዳንድ ሰዎች «እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ የሚገኘው እርሱ በፍጥነት ሁሉም ስፍራ ስለሚሮጥ ነው» ብለው ያስባሉ።

- ይህ እውነት አይደለም።

- አሁንም አንዳንድ ሰዎች ደግሞ «እግዚአብሔር ሁሉም ስፍራ የሚገኘው ምድርን የሚሞላ ግዙፍ አካል ስላለው ነው» ብለው ያስባሉ።

- ይህም እውነት አይደለም።

- አሁንም አንዳንድ ሰዎች «እግዚአብሔር ሁሉም ስፍራ የሚገኘው እርሱ በምድር ሁሉ ላይ ስለሚቀመጥ ነው» ብለው ያስባሉ።

- ይህም ደግሞ እውነት አይደለም።

- የእግዚአብሔር መጽሐፍ «እግዚአብሔር መንፈስ መሆኑንና ሁል ጊዜ በሁሉም ስፍራ እንዳለ ይናገራል።

- እግዚአብሔርን የሚመስለው ማንም የለም።

- ሁል ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኘው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- የትም ስፍራ ብንሄድ፣ እግዚአብሔር በዚያ አለ።